# ሞትም ወንድ መራጭ ነው





ክፉትና ደጉን ለይቶ የሚያውቀው፤
ቅዱስ ተጠግቶ ሰይጣን እሚሸሸው፤
ሰዎች ብቻ አይደሉም ሞትም ደግ ወዳጅ ነው።

ለሕዝብ ልእልና የተሟገቱትን፣
ለነሱ ሳይኖሩ ለሰው የኖሩትን፤
ተሻምቶ ይወስዳል ተማምኖ ጉልበቱን፤
ይግባኝ የት ይባላል ማን ይከሳል ሞትን?

ገፎ እየወሰደ ልብስ ጥላችንን፤
ከፀሐይ ከዝናብ የሚከልሉንን፤
ሞት ፍርደ ገምድሉ ራቁት አስቀረን።

ገዳይ አስገዳዩ ጓዙ እየከበደው፤
ይዞ ለመኮብለል እሚሽቀዳደመው፣
በምድር ላይ ተንኮል ያልፈጸመውን ነው።

ሀዲስን እናዝግም ፀጋን እሩጥ አለው፣
አስራትን እንሂድ መኩን ቶሎ ና አለው፤
ሰዎች ብቻ አይደሉም ሞትም ሰው ጋባዥ ነው።

እርሱም እንደ ጨዋ ከንቱ ሰው አይወድም፤
አብሮ እድር አይጠጣም እቁብም አይበላም፤
ሲመጣ አያስከትል ሲሄድ ይዞ አይሄድም።

ለፍትህ ተዋጊን በባትሪ ፈላጊው፤
በማተቡ አዳሪን አባሮ እሚይዘው፤
ብዕረ-ርትኡን ይዞ የሚነጉደው፤
ሴቶች ብቻ አይደሉም ሞትም ወንድ መራጭ ነው።





*ሲጋችሁን ብዕር፤ ነፍሳችሁን ደግሞ ፈጣሪ ለዘላለም ያወድሰው።*

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ተጻፈ የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ. ም.
ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ (አሜሪካ)